# <u>የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 940/2015 ለመሻር በተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ የቀረበ አጭር ማብራሪያ</u>

በሀገራችን የግንባታ ዘርፍ ማደግን ተከትሎ የሲሚንቶ ገበያ በተለያዩ ምክንያቶች በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ እና ሥርጭቱ እየተስተጓጎለና የዋጋ ንረቱ እየተባባሰ በመሄዱ የሲሚንቶ ገበያውን ለማረጋጋት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶ ግብይትን በተመለከተ መመሪያ ቁጥር 908/20143 አውጥቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ከቆየ በኋላ መመሪያው በተግባር ሲፈተሽ ሲሚንቶን በቀጥታ ከፋብሪካው የመግዛት እድል ያገኙ አካላት በዋጋም ሆነ በአቅርቦት ተጠቃሚ መሆን የቻሉ ቢሆንም በተመረጡ አቅራቢዎች ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የተደረገው የሲሚንቶ ሥርጭት የተጠቃሚውን ፍላጎት ያላሟላ ከመሆኑም በላይ ለተለያዩ ህገወጥ አሠራሮች የተጋለጠ መሆኑን በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል ከተካሄደው የአፈፃፀም ፍተሻ ጥናት እንዲሁም ከህብረተሰቡና በዘርፉ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት የቀረቡ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን በግብዓትነት በመውሰድ የቀድሞውን መመሪያ የተካውን አሁን በሥራ ላይ ያለውን የሲሚንቶ ግብይት መመሪያ ቁጥር 940/2015 አውጥቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የተሻለ አቅም ያላቸው የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወደ ማምረት ሥራ እየገቡ በመሆኑ ዘርፉን ለገበያው መተው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሥራ ላይ ያለውን የሲሚንቶ ግብይት ለመቆጣጠር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 940/2015 መሻር አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ይህ የመሻሪያ መመሪያ ተዘጋጅቶ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ከዳበረ በኋላ ለበላይ አመራሩ ቀርቦ ይሁንታ ተሰጥቶበት እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡

ስለሆነም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመመሪያውን አስፈላጊነት ተገንዝቦ በአስተዳደር ሥነሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሠረት እንዲመዘግብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner

## መመሪያ ቁጥር 1035/2017

## የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣውን መመሪያ ለመሻር የወጣ መመሪያ ቁጥር 1035/2017

የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣውን መመሪያ ቁጥር 940/2015 መሻር በማስፈለጉ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሲሚንቶ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ መሻሪያ መመሪያ ቁጥር 1035/2017"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2.. **ስለመሻር**

የሲሚንቶ ግብይት ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 940/2015 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

3. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ 11 ቀን 2017 ዓ.ም

ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner

## DIRECTIVE NO. 1035/2025

## A DIRECTIVE ISSUED TO PROVIDE FOR THE REPEALING OF CEMENT MARKETING CONTROL DIRECTIVE No. 1035/2025

WHEREAS, it has been found necessary to repeal Cement Marketing Control Directive No. 940/2023;

NOW, THEREFORE, the Ministry of Trade and Regional Integration has issued this Directive pursuant to the provisions of Article 19 (4) of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263 /2021.

1. **Short Title**

This directive may be cited as the **"Cement Marketing Control Directive Repealing Directive No. 1035 /2025."**

2. **Repeal**

Cement Marketing Control Directive No. 940/2023 is here by repealed.

3. **Effective Date**

This Directive shall come into force on the date of its registration by the Ministry of Justice and upon uploading on the website of the Ministry.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of December 2024**

**KASSAHUN GOFE BALAMI (Ph.D.)**

**MINISTER OF TRADE AND REGIONAL INTEGRATION OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade and Regional Integration
Archives
መዝገብ ቤት

CamScanner